# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ
# ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኦክቶበር 21-31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከኖቬምበር 1-10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኖቬምበር 2022
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........ 1

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ........ 2

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት........ 3

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ........ 4

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር........ 4

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ........ 5

በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 5

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ........ 5

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ 6

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 6

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ........ 7

ሁኔታ አዝማሚያ........ 7

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 1 እስከ 11, 2022 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ. ........ 7

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 1 እስከ 11, 2022 ........ 7

የሚኖረዉ ዝቅተኛ የአየር ሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺየስ ........ 7

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 22 እስከ ኖቬምበር 1, 2022 የሚኖረዉ ዝናብ በሚ.ሜ መጠን በሚ.ሜ........ 7

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 8

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 8


# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በምስራቅ አማራ፣ ትግራይ እና አፋር ክልሎች፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖባቸዉ ተስተዉሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በተጠቀሱት የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ አልፎ አልፎ የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ ጨምሮ ተስተዉሏል፡፡ በተጨማሪም የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀት መጠን በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ ከ5 ዲ.ሴ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነትም በደብረ ብርሀን 1.8፣ 1.2 እና 2.2፣ በወገልጤና 1.8 እና 3.0፣ በቡኢ 3.8፣ በጨፋ 4.0፣ በእነዋሪ 4.6 እና 4.5፣ በፊቼ 4.2 እንዲሁም በመሀል ሜዳ 1.8 እና 3.0 በዲ.ሴ ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተሻለ የደመና ሽፋን ከመኖሩ ጋር ተያይዞ በምዕራብና ደቡብ ኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ በምዕራብ ኢትዮጵያ እንዲሁም በደቡብ ሱማሌ አካባቢዎች ላይ በተለይም በመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናት ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በደቡብ ሱማሌ፣ በጋምቤላ እና በደቡብ ኦሮሚያ በጥቂት ስፍራዎቻቸዉ ላይ ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በአርባ ምንጭ 41.7፣ በአይከል 46.3፣ በባህር ዳር 35.8፣ በዶሎመና 30.3፣ በጊኒር 32.0፣ በሀገረማርያም 46.7፤ በቀብሪደሀር 50.2፤ በነጆ 40.5 እንዲሁም በጊዳ አያና 63.3 በሚሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የነበረው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከአማራ የምዕራብና መካከለኛው ጎንደር፤ የአዊና የምዕራብ ጎጃም፤ የቤንሻንጉል-ጉምዝ፣ የጋምቤላና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከኦሮሚያ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ የኢሉአባቦራ፣ የቡኖ በደሌ፣ የጅማ፣ የጉጂና ቦረና፣ የምዕራብ አርሲና አርሲ፣ ምስራቅ ሀረርጌ እንዲሁም የባሌ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል እንዲሁም በሱማሌ ሁሉም ዞኖች ላይ ከ5-105 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-11 ቀናት ያህል ነበራቸዉ (ከርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር ከአማራ የምዕራብና መካከለኛው ጎንደር፤ የአዊና የምዕራብ ጎጃም፤ አብዛኛው የጋምቤላና የቤንሻንጉል-ጉምዝ ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከኦሮሚያ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ የኢሉአባቦራ፣ የቡኖ በደሌ፣ የጅማ፣ የጉጂና ቦረና፣ የምዕራብ አርሲና አርሲ፣ ምስራቅ ሀረርጌ እንዲሁም የባሌ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል እንዲሁም በሱማሌ ሁሉም ዞኖች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ መጠን የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት አካባቢዎች ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 3)።


ካርታ 1 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች　　　　መደበኛ　　　　ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው የኦክቶበር የመጨረኛዎቹ አስራ አንድ ቀናት ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሰሜን አጋማሽ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖ እንደነበረ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም በመሆኑም በተለይም በመደበኛ ሁኔታ ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍል ዝናብ መውጫው ስለሆነና በዚህ ጊዜ የሰብል ስብሰባቸውን በሚያካሂዱ በአንዳንድ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች የነበረው ደረቅ የአየር ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባው አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ቢሆንም፤ በአንዳንድ ለውርጭ ተጋላጭ በሆኑ ሥፍራዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እየጨመረ በመምጣቱ እድገታቸውን ባልጨረሱ ሰብሎች እና በመስኖ በሚለሙ አትክልቶች ላይ በተወሰነ መልኩ አሉታዊ ተፅእኖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች በተለይም በመጀመሪያዎቹ አምሰት ቀናት ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ በመኖሩ ምክንያት የተገኘው እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና አልፎ አልፎ ፍሬ በመሙላት ላይ ለነበሩ የመኸር ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ገንቢ ሚና የነበረው ሲሆን፤ በአንጻሩም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው በመሆኑ የተገኘዉ እርጥበት ጥምር ግብርና ለሚካሄድባቸው በደቡብ ደጋማ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ለተዘሩ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በቆላማው አካባቢ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲሁም የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማቸት ጥሩ አጋጣሚን የፈጠረ ነበር (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው የኦክቶበር የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት በደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት የተስተዋለበት እንደነበረ የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህንን ሁኔታ ተከትሎ በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኦጋዴን፣ የመካከለኛው እና የታችኛው ዋቤ ሸበሌ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ባሮአኮቦ እንዲሁም የላይኛው እና የታችኛው አባይ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛው አባይ ኪስ ቦታዎች፣ በታችኛው ባሮ አኮቦ እና በጥቂት የመካከለኛው ተከዜ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት ተፋሰሶች በደረቅ እና በከፊል ደረቅ ሁኔታ ስር ቆይተዋል (ካርታ 5) ፡፡


ካርታ 5 ኢ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21 እስከ 31/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቨምበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝን ሲሆን፤ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፣ በደቡብ ምሥራቅና በመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አነስተኛ ዝናብ ይዘወተራል፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛው የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተጨማሪም በአንዳንድ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ሊጠናከር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ከዚህም ሌላ ከኦሮሚያ ዞኖች ምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምሥራቅ ሐረርጌ፣ እንዲሁም አርሲና ምስራቅ አርሲ፣ የጉጂና ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ እንዲሁም የቦረና ዞኖች፤ የጋምቤላና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የወላይታ፣ የደቡብ ኦሞ እና የሰገን ሕዝቦች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የከፋና የቤንች ማጂ፤ ከሱማሌ ክልል የአፍዴር፣ የዳዋ እና የሊበን ዞኖች በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 1 እስከ 11, 2022 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 1 እስከ 11, 2022 የሚኖረዉ ዝቅተኛ የአየር ሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺየስ

## ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ የሚስተዋል ሲሆን፤ በሌላም መልኩ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምስራቅ እንዲሁም በመካከለኛው አካባቢዎች ላይ መጠነኛ የሆነ እርጥበት የሚያገኙበት ጊዜ ነው፡፡

በሚቀጥሉት የኖቬምበር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛው የበጋው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚያመዝን የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በተለይም የመኸር ሰብል ለሚሰበስቡና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለሚያከናውኑ አካባቢዎች አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮች ይህንኑ ምቹ ሁኔታ ከግምት በማስገባት የደረሱ ሰብሎችን በአግባቡና በጊዜው እንዲሰበስቡ ይመከራሉ፡፡ በተጨማሪም ከደረቃማው ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በአንፃራዊ ሁኔታ ሊጠናከርና በአንዳንድ አካባቢዎችም ውርጭ የመከሰት እድል ስለሚኖረው ይህም ሁኔታ እድገታቸውን ባልጨረሱ ሰብሎችና በመስኖ የሚለሙ ተክሎችን ሊጎዳ ስለሚችል አርሶ አደሮች አስፈላጊውን ጥንቃቄ ለማድረግ እንዲችሉ የግብርና ባለሙያዎች ቅርብ ክትትልና አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርጉ ከወዲሁ ይመከራል፡፡ በሌላም በኩል ከሚጠናከሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በተለይም የምዕራባዊና የደቡባዊ አጋማሽ በተጨማሪም ምሥራቅ ሐረርጌ፣ አርሲና ምስራቅ አርሲን ጨምሮ በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ ቀላል መጠን ያለው የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ይህም የሚጠበቀው እርጥበት በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸርና የበጋ ወቅት ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት በጎ ሚና ይኖረዋል፡፡

## ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኖቨምበር ወር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በምዕራብ በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ይህንን ተከትሎ በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ ገናሌዳዋ፣ የመካከለኛው እና የታችኛው ዋቢሸበሌ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ እና ኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ መጠነኛ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በመሆኑም በእነዚህ ተፋሰሶች ላይ የሚገኘውን እርጥበት በተለያየ ዘዴ ውሃን በመሰብሰብ ዘለቄታ ጥቅም እንዲኖረው ለማድረግ ያስችላል፡፡ የተቀሩት የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ እንዲሁም የመካከለኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በአብዛኛው በበጋው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ስር እንደሚቆዩ ይጠበቃል።